የኢትዮጵያመገናኛ ብዙሐን / ጋዜጠኞችአጀንዳዎችንለሀገራዊውይይት

ከኢትዮጵያሚዲያካውንስል

ለ፡የኢትዮጵያብሄራዊምክክርኮሚሽን

አዲስ አበባ ፤ ኢትዮጵያ

ቀን ጥር 01/2017 ዓ.ም National Dilogue

መግቢያ፡

ብሄራዊ ምክክር የኢትዮጵያን ስር የሰደዱ ማህበረ-ፖለቲካዊ ተግዳሮቶችን ለመፍታት፣ እርቅን፣ አንድነትን እና ዘላቂ ሰላምን ለማምጣት ወሳኝ መድረክ ሆኖ ያገለግላል። ለምሳሌ፣ የደቡብ አፍሪካ የእውነት እና የዕርቅ ኮሚሽን እና የቱኒዚያ ብሔራዊ ውይይት ኳርት ጥልቅ የተደራጁ ውይይቶች በማድረጋቸው መለያየትን አስቀርተው፣ አንድነትን በማምጣት፣ ሀገራዊ ቀውስን ወደ ብሔራዊ ፈውስ በመቀየር በምሳሌነት ይነሳሉ። ከእነዚህ አብነቶች በመነሳት፣ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምክክር ልዩ ተግዳሮቶችን ለመፍታት ትልቅ አቅም አለው። በኢትዮጵያ ውስብስብ እና የተከፋፈለ የመገናኛ ብዙሃን መልክዓ ምድር፣ ሚዲያው እድልም፣ ችግርም እንደሆነ እና ድርብ ሚና እንዳለው እነገነዘባለን፡፡ በመልካም ጎኑ ስናየው የህዝብን ድምጽ ያሰፋል፣ በመረጃ ላይ የተመሰረተ ንግግርን ያመቻቻል፤ የሀሳብ ብዝሀነትን እና መግባባትን ያመጣል፣ የስርዓት ጉደለቶችን ይታገላል፡፡ ይጠይቃል፣ ያስጠይቃል፣ ግንዛቤ ይፈጠራል፣ የጠራ ውሳኔ እና ግልፅነት እንዲኖር በር ይከፍታል፡፡ በተቃራኒም የተገነባ ያፈርሳል፡፡ ለአለመግባባት ምንጭ ይሆናል፡፡ የታነፀ ያወድማል፡፡

በአገር አቀፍ የምክክር ሂደት ውስጥ እንደ ሸምጋይ እና ተሳታፊ ሆኖ እንዲያገለግል የሚዲያ ዘርፉን ማጠናከር ወሳኝ ነው። የኢትዮጵያ መገናኛ ብዙሐን ምክር ቤት ከ102 የሚበልጡ የሚዲያ ተቋማትን በመወከል እነዚህን ችግሮች ለመፍታት እና የለውጥ ተሃድሶዎችን የማበረታታት ኃላፊነት ተሰጥቶታል። ይህ ሰነድ በኢትዮጵያ ውስጥ ያሉትን ዋና ዋና የሚዲያ ተግዳሮቶች በጥልቀት ያብራራል፣ ተጽኖአቸውን ይዘረዝራል እና ተግባራዊ ሊሆኑ የሚችሉ መፍትሄዎችን ከህግ እና ከተመዘገቡ ምንጮች ጋር በማጣቀስ ያቀርባል። በለያቸው አምስት ዋና ዋና ጉዳዩች ሰፊ፣ የብዙ አካላት ውይይት እና ኃላፊነት ፣ ከብሄራዊ ምክክር ከሚጠበቁ ግቦች ጋር ተሰናስለው ቀርበዋል፡፡

የመግናኛ ብዙሐን ምክር ቤት እይታ

ምክክር ተወካዮች ስለማይግባቡባቸው ነገሮች በጋራ በመወያየት መግባባት ላይ ለመድረስ የሚያደርጉት ሂደት ነው፡፡ በሀገራችም አንዱ የማይግባቡ እና የማያፍባቡ መንገዶችን በመፍጠር እና ሰፊ ሚናዎችን በመጫዎት ቁልፍ አስተዋፅኦ ሊደረግባቸሰው የሚገቡት የሚዲያው ክፍል ነው፡፡ የመገናኛ ብዙሐን ምክርቤቱም በተለየ ሁኔታ አካታች በሆነ መንገድ እናበርካታ ባለድርሻ አካላት የሚሳተፉበት ሁነት በማዘጋጀት ፣ መጀመሪያ በባለቤትነት፣ በብሄር ፣ በሃይማኖት ፣ በፖለቲካ ርዕዮት አለም፤ በአካባቢ ፣ በቋንቋ ፍጥጫ ውስጥ የገቡት የሀገር ውስጥ መገናኛ ብዙሐን ምክክር የሚያደርጉበትን መንገድ ቀይሶ የድርሻውን ለመወጣት እየሰራ ይገኛል፡፡ በውይይቱ በገለልተኛ እና ብቁ በሆኑ አወያዮች እና አመቻቾች በተመራ አሳታፊ የምርምር እና የውይይት ማዕቀፍ አጀንዳዎችን ለይቷል፡፡

በእርግጥም በሀገሪቱ የገባችብትን ችግር ለመታደግ የተቋቋመው ኮሚሽን ምክክርን መሰረት አድርጎ ሲመጣ የመገናኛ ብዙሀን ቀዳሚ አላማም የምክክር አማራጭ ሁኖ ለብዙሐኑ መቅረብ እና የጋራ መግባባትን መፍጠር ቀዳሚ ድርሻው እንደሆነ እሙን ነው፡፡ ከሌሎች የግጭት መፍቻ መንገዶች በተለየ መልኩ በተወሰኑ ጉዳዮች ላይ መስማማት ላይ ብቻ የሚያተኩር ሳይሆን ተጨባጭ ለሆኑ እና በመተማመን ለሚፈጥሩ መግባባቶች መደላድል የሚፈጥር ነው፡፡ ምክክር ረጅም ጊዜን የሚወስድና በውጤቱም መሰረታዊና መዋቅራዊ ለውጥ ላይ ያተኮረ አማራጭ እንደሆነ ይታመናል፡፡

በእርግጥም ምክረ ሀሳብ ማቅረብ ላይ ብቻ ትኩረት የሚያደርግ እንደመሆኑ መጠን በሙያ የተደራጁ ተቋማት የሚያቀርቧቸው ግበዓቶች በችግሩ ውስጥ የታለፉ እንደመሆኑ መጠን የመፍትሄ ግበዓት ለመሆን ድርሻቸው ሰፊ ነው፡፡ ምክረ ሀሳቦቹን የመፈፀም ኃላፊነት የሚመለከታቸው ህግ አውጭ፣ አስፈፃሚ እና ተርጓሚ ኃላፊነት እንደመሆኑ መጠን የበኩላችንን ድርሻ ለማስደመጥ እና ለመደመጥም እድል የሚሰጥ ሁኖ አግኝተነዋል፡፡

የሚደረስባቸው የፖለቲካ እልባቶች ከውስን የልሂቃን ፍላጎት ባሻገር የህዝብን ጥቅም በፍትሃዊነት የሚያስከብሩ በመሆናቸው ዘላቂ ሰላም ለመፍጠር ብርቱ አቅም አላቸው፡፡ እንደብዙሐን ተቋምነታችን እኛም በምናደርገው ተሳትፎ የሃሳብና የፍላጎት ብዝሃነት

በሚያይልባቸው እንደ ኢትዮጵያ ባሉ ሀገራት የውስን ልሂቃን ፍላጎት አጀንዳውን በመቆጣጠር ሌሎችን እንዳይጨፈልቅ የማድረግ አቅምን ይፈጥራል።

አምስቱ የመገናኛ ብዙሐን አጀንዳዎች

አጀንዳ 1፡ የህዝብ ሚዲያ አስተዳደር

የአጀንዳው ፅንሰ ሃሳብ፡-የህዝብ ሃብት የሆኑ መገናኛ ብዙሐን በሀገር አቀፍ ደረጃ የተቋቋሙ እና በክልሎች የፖለቲካ አሰተዳደር ስር ያሉት ሚዲያዎች የብሄራዊ መግባባት የችግር ምንጭ ናቸው።።የሕዝብሚዲያአስተዳደርናማሻሻያ፡- መንግሥትበሚያስተዳድራቸው እና የህዝብ ንብረት የሆኑ የሚዲያተቋማትውስጥየሚስተዋለዉየፖለቲካላልቃገብነቶች፣ የዴሞክራሲ ተቋምነት ህልውና አሳጥተዋል። የግልጽነትእጦት ፈጥረዋል። በአስፈፃሚው መልካም ፈቃድ ስር ወድቀዋል።።የሀብትኢፍትሃዊነትንለግለ ሚዲያ ተሳትፎ ስራን በማያበረታቱ ሁኔታ በወራሽነት የህዝብን ገንዘብ በመውስድ ከፍትሃዊ ውድድር ውጭ ሁነዋል።።በህዝብ ሚዲያዎች ባለቤትነት እና አሰተዳደር ክፍተት ምክንያት የፖለቲካ ርዕዩት አራማጅ ፣ የብሄር ወይም የክልል ጆኦግራፊን አሰፋፊር የሚከተለ በመሆኑ ከሚዲያ አሰያየም ጀምሮ፣ አሰተዳደር እና ሹመት በፈጠረው ችግር ለብሄራዊ መግባባት እንቅፋት በመሆናቸው የውይይት አጀንዳ በመሆን መፍታት አለበት።

የአጀንዳው ማብራሪያ፡-ችግሮች በዝርዝር

1. **የፖለቲካ ጣልቃገብነት፡-** የመንግስት የሚዲያ ተቋማት በፖለቲካ አጀንዳዎች ከፍተኛ ተጽዕኖ ይደረግባቸዋል። የአሰራር አዋጃቸው ይጣሳል። የዴሞክራሲያዊ ተቋምነታቸው አይከበርም። በመንግስት ሚዲያዎች ውስጥ የአመራር ቦታዎች ብዙውን ጊዜ በፖለቲካዊ ግንኙነት ባላቸው ግለሰቦች የተሞሉ ናቸው። በዚህም ምክንያት የአርትኦት ነፃነት እጦት፣ የጋዜጠኞች ነፃነት፣ ለህዝብ አገልጋይነት ችግር ይከሰታል።።ማሰረጃዎች እንደሚያመለክቱት በወሳኝ ኩነቶች ወቅት የህዝብ መገናኛ ብዙሃን የተቋዋሚዎችን ድምጽ እና አማራጭ አመለካከቶችን በማግለል፣ በማፈን እና የአንድን ወገን ድምፅ ብቻ በማሰማት፣ ለገዥው ፓርቲ አንደበት ሆነው ያገለግላሉ። በዚህም በሀገሪቱ በግሉ እና የመንግስት መገናኛ ብዙሐን ጤናማ ያልሆነ ፉክክር እና የመረጃ ፍሰት ብሄራዊ መግባባቱ የተዛነፈ እንዲሆን አድርገውታል። ለአብነት ያህል በ2021 የኢትዮጵያ ሀገራዊ ምርጫ የህዝብ መገናኛ ብዙሀን ዘገባ ተመጣጣኝ ባልሆነ መልኩ ገዥው ፓርቲ ያስመዘገባቸውን

ስኬቶች በማጉላት ለተቃዋሚ እጩዎች የአየር ሰአት የተወሰነ ጊዜ ሲሰጥ ነበር። በተመሳሳይም በትግራይ ግጭት ወቅት በመንግስት የሚተዳደሩ ተቋማት በዋነኛነት የመንግስት ትረካዎችን በማስተጋባት ከተጎዱ ክልሎች ነፃ ትንታኔዎችን እና አመለካከቶችን ወደ ጎን በመተው የሙያ ነፃነታቸው ተጥሶ። እነዚህ አሠራሮች ለአድሎአዊ አመለካከት እንዲዳብሩ እና ህዝቡ በመንግስት ሚዲያ ተቋማት ላይ ያለውን እምነት እንዲቀንስ አድርጓል።የመገናኛብዙሃንአዋጅቁጥር 1238/2013 ንዑስክፍልሁለትላይየመገናኛብዙሃንግዴታዎችበሚለውድንጋጌሥርበግልጽእንደተቀመጠው መገናኛብዙሃንበሀገሪቱሕገመንግስትናየምርጫሕግመሠረትየሚንቀሳቀሱየፖለቲካፓርቲዎችን ወይምድርጅቶችንበፍትሐዊነትየማገልገልግዴታአለባቸውየሚልቢሆንም፤ ይህንን አይተገብሩም።

ለአብነተም በ1990ዎቹአጋማሽከ 480 በላይጋዜጦችእናመጽሔቶችህዝብጋርይደርሱእንደነበረየመገናኛብዙሃንባለስልጣንመረጃዎችያ ሳያሉ። በአሁኑ ስዓት ባለው ጣልቃ ገብነት በቁጥር እጅግ አነሰተኛ የሆኑ የህትመት ሚዲያ ቀርተዋል። በመቶዎች ከገበያ ወጠው ቁልፍ የሆነው ዘርፍ የፖለቲካ ተዕኖው እንቅፋት ሁኗል።

2. **የአመራር ሹመት ሂደት፡-** የህዝብ መገናኛ ብዙሃን የአመራር ምርጫ ሂደቶች ግልጽነትና ሁሉን አቀፍነት የጎደላቸው ናቸው። በ2021 የኢትዮጵያ አጠቃላይ ምርጫ የመንግስት ሚዲያዎች ባልተመጣጠነ መልኩ በመንግስት ትረካዎች ላይ ያተኮሩ ናቸው (ፍሪደም ሃውስ፣ 2022)።በፖለቲካ ተነሳሽነት የተሾሙ ሹመቶች ገለልተኝነትን እና የህዝብን እና የሀገርን ፍላጎት አያረጋግጡም። በመገናኛ ብዙሐን 2020 ፖሊሲም ሆነ በመገናኛ ብዙሐን አዋጅ ቁጥር 1238/2013የሕዝብመገናኛብዙሃንየአመራርምደባሙያዊብቃትንናየዓታስብጥርን፣ብዝሃነትንና ገለልተኛነትንመሰረትያደረገመሆንይኖርበታል።የሕዝብመገናኛብዙሃንእውነተኛየሕዝብመገና ኛብዙሃንነቱንለማረጋገጥዴሞክራሲያዊ ተቋምነቱ እንዲከበር የፖለቲካ ማሻሻያ እና ምክክር አጀንዳ ሁኖ መቀርብ ይኖርበታል።

3. **የህዝብ ገንዘብ አሰተዳደር ችግር እና የመልካም አስተዳደር እጦት፡-** የህዝብ መገናኛ ብዙሀን ፍትሃዊ ባልሆነ የሃብት ድልድል ይሰቃያሉ። በመንግስት ቁጥጥር ስር ያሉ ማሰራጫዎች የማስታወቂያ ገቢዎችን እና የመንግስት ድጎማዎችን በብቸኝነት

ይቆጣጠራሉ፣ ይህም የግል እና የማህበረሰብ ሚዲያዎች ግብር ከፋይ ሁነው የሚሰሩ እና የማህበረሰብ እና ሀገር ግንባታ ያላቸው ድርሻ ትኩረት በመንፈግ፣ የጥላቻ ትርክት በመፍጠር እንዲገለሉ እናፍትሃዊ የህዝብ ሀብት እንዳያገኙ አድርጓል። በተጨማሪም፣ የፋይናንስ ነፃነት እጦት የሕዝብ መገናኛ ብዙሃን ለመጠቀሚያነት ተጋላጭ፣ ነፃ ሚዲያ፣ ገለልተኛ እና ተወዳዳሪ እንዳይሆኑ ሁነዋል።

4. **የቁጥጥር ድክመቶች፡-** ተቆጣጣሪ አካላት በፖለቲካ ጣልቃ ገብነት ምክንያት ገለልተኛነትን ማስከበር ተስኗቸዋል። የኢትዮጵያ ብሮድካስት ባለስልጣን ራሱን ችሎ መስራት አለመቻሉ ችግሩን አባብሶታል (የኢቢኤ አመታዊ ሪፖርት፣ 2021)።

5. **የክልል የህዝብ መገናኛ ብዙሐን ከስያሜ እስከ አካባቢያዊ የፖለቲካ ከፍተኛ** ቁጥጥር የተያዙ በመሆኑ በሀገር አቀፍ ደረጃ የሙያውን እድገት የሚገድብ እና ሀገራዊ ቀውስን በሚጨምር ሂደት ላይ ናቸው።።የኢትዮጵያየመገናኛብዙኃንተቋማትከጎሳናከፖለቲካዊወገንተኝነትበመላቀቅ፣የአገርን ብሔራዊጥቅምለማስከበር እንዲሰሩ ምክክር ሊደረግባቸው ይገባል።።

የነዚህም ተፅዕኖዎች ሲገለጥ፡

• የነጻ ፕሬስ እና ብዝሃነትን ማፈን።

• የህዝብ ሚዲያ እንደ ታማኝ የመረጃ ምንጭ አለመተማመን።

• ዴሞክራሲያዊ ንግግርን ማፈን።

አውንታዊ ምክሮች

1. ወደ ፐብሊክ ሰርቪስ ሚዲያ መሸጋገር፡ ከቢቢሲ ጋር የሚመሳሰሉ የአስተዳደር ሞዴሎችን መቀበል፣ የአርትኦት ነፃነት እና የህዝብ ተጠያቂነት ላይ አፅንዖት መስጠት እና መስራት ያስፈልጋል።

2. ግልጽ የአመራር ምርጫ፡- ከሲቪል ማህበረሰብ እና ከሚዲያ ባለሙያዎች ውክልና ያለው ለአመራር ሹመቶች ገለልተኛ የበላይ አካል ማቋቋም እና የዴሞክራሲ ተቋምነቱን ፖለቲካዊ የሚያከበረው እና ተጠያቂነቱን ለመወጣት ዝግጁ መሆን አለበት።

3. የፋይናንሺያል ማሻሻያ፡- ፍትሃዊ የገንዘብ ድጋፍ ዘዴዎችን ማዘጋጀት እና የሃብት ክፍፍልን ማረጋገጥ ያስፈልጋል።

4. የቁጥጥር ማዕቀፎችን ማጠናከር፡- የኢትዮጵያ ብሮድካስት ባለስልጣን ከበርካታ ባለድርሻ አካላት የቦርድ ክትትል በማድረግ ራሱን ችሎ እንዲንቀሳቀስ ማድረግ አለበት።

አጀንዳ 2፡ መረጃ የማግኘት መብት፣ ስርጭት እና ተደራሽነት

የአጀንዳው ፅንሰ ሃሳብ፡-የመረጃተደራሽነት፡- በሕዝብመረጃተደራሽነትላይገደቦች፣ የመረጃ ክልከላ የኢንተርኔትመዘጋትእናየአስተዳደርግልጽነትእጦት በመኖሩ ህዝብ የሚፈለገውን መረጃ በትክክለኛ ስዓት እና ቦታ አያገኝም፡፡ በዚህም ምክንያት ለሀሰተኛ መረጃ እና ለጥላቻ ንግግር በር ከፍቶ ለህዝቦች ግንኙነት እንቅፋት እየሆነ ይገኛል፡፡ በሀገሪቱ ለሚታየው ተጠያቂነት መጉደል፣ ኃላፊነትን መወጣት እንቅፋት በመሆኑ በሐገራዊ ምክክሩ ሂደት ከህግ ማዕቀፍ ስሪት እስከፖለቲካ ቁርጠኛ የውሳኔ ለውጥ ወይይት ቢደረግበት ሀገራዊ ችግሮችን በዘላቂነት ለመፍታት አሻራ ይኖረዋል።ስንል በአጀንዳነት አቅርበነዋል፡፡

የአጀንዳው ማብራሪያ፡-መረጃ ማግኘት የሚዲያዎች ፈተና ሁኗል፡፡ በዚህም ምክንያት ለዘመናትአብሮበኖረውህዝብመሀልአንድነትንየሚሸረሽር፤እርስበእርስበጥርጣሬእንዲተያይየሚ ያደርግከፋፋይየሆኑንግግሮች፤መግለጫዎችናሀሳቦችበመገናኛብዙኃንአማካይነትበስፋትሲሰራ ጭተመልክቷል፡፡
አንዳንዶቹአለፉታዊይዘትያላቸውንግሮችናመግለጫዎችበመንግስትባለስልጣናት፤በፖለቲካፓር ቲአመራሮች፤በሀይማኖትሰባኪያንናበምሑራንመደረጉንስንመለከትመገናኛብዙኃንበሕጉአግባ ብሙያዊነፃነታቸውንተጠቅመውስራቸውንከፍባለየኃላፊነትደረጃለማከናወንየመረጃ አቅርቦት ፍትሃዊ አለመሆን አጀንዳ እንዲሆን ያስገድዳል፡፡

መገናኛብዙኃንበሕገመንግስቱ አንቀፅ 29ሆነሀገሪቱፌርማበተቀበለቻቸውዓለምአቀፍፕሮቶኮሎችመሠረትየሕዝብን አንድነትየሚንዱ፣ ጥላቻንናግጭትንየሚያባብሱንግግሮችናድርጊቶችንማሰራጨትየለባቸውም፡፡ንግግሮቹበማንም ይነገሩበማን ያለፉቋሎችንከሚቀሰቅሱ፣ጥላቻንከሚያነግሡ፣ሕዝብበጥርጣሬእንዲተያይየሚያ

ደርጉና፣የሀገርንሰላምናደኅንነትአደጋላይየሚጥሉመልዕክቶችንከማሰራጨታቸውበፊትአስፈላጊ ውንየአርትኦትስራሊሰሩባቸውእንደሚገባ ይደነግጋል፡፡

የኢትዮጵያየጥላቻንግግርእናየሀሰትመረጃመከላከልናማፈንአዋጅቁጥር 1185/2020 እንደተቀመጠውመገናኛብዙኃንበዘገባዎቻቸውማናቸውንምየህብረተሰብክፍልበዘር፣በብሔር፣በ ያታ፣በሃይማኖትወይምበፖለቲካዊአስተሳሰብንመሠረትበማድረግየሚሰጥ/የሚነገር/ ጥላቻንየሚያበረታታ፣ሰብአዊክብርንየሚያዋርዱየአደባባይመግለጫዎችን፣ንቀትንወይምመገ ለልንሊፈጥርየሚችልቋንቋንየሚጠቀሙእንግዶችንከመጋበዝእናከፋፋይመግለጫዎችንምበማህ በራዊሚዲያጭምርከማሰራጨት የሚቆጠቡት አንድም ለሙያው ሰነ ምግባር ተገዥ መሆናቸው የሚረጋገጠው በቂ የመረጃ አቅርቦት እና አሰገዳጅ አሰራር ሲኖር ነው፡፡ ችግሮች በዝርዝር

1. የመረጃ ገደቦች፡- ጋዜጠኞች በቢሮክራሲያዊ አሰራር ክልከላዎች እና ገዳቢ ህጎች ምክንያት የህዝብ መረጃን ለማግኘት እና ለህዝብ ለማድረስ ከፍተኛ እንቅፋት ይገጥማቸዋል።የኢትዮጵያየጸረሽብርተኝነትህግሽብርጋርየተያያዘውስለሽብርየሚያወ ራውየኢትዮጵያህግየኢትዮጵያየፀረ-ሽብርተኝነትአዋጅቁጥር 652/2001 አዋጅን በመንተራስ የጸረ-ሽብርተኝነት ህግን በተደጋጋሚ መረጃን ለመደበቅ መጠቀሙ ግልጽነት የጎደለው መሆኑን ያሳያል።በዚህወቅትለፕሬሶችየሥነምግባርመርህንየያዘመረጃለኅብረተሰቡበአግባቡባለ መሰጠቱሕዝቡበትክክለኛውመንገድለአገርግንባታ፣ለሰላም፣ለልማትከመሳተፍይልቅሚ ዲያውበሚሰጠውየተሳሳተመረጃወደግጭት፣መራራቅ፣ይህንንምተከትሎወደሰላምዕጦት ውስጥ እንዲገባ የራሳቸው አስዋፅኦ አድርገዋል፡፡

በዚህም ብሄራዊ ምክክሩ በአጀንዳነት አዲስ የመረጃ ነፃነት አዋጅእስከማፀደቅ የሚደርስ እና አሰገዳጅመረጃየማግኘትመብትንእናየህዝብንጥቅምየሚያስጠብቅእናበአሁኑወቅት ያለውንየመ ረጃብክለትእናሀሰተኛመረጃንለመከላከልአይነተኛመሳሪያሁኖየሚያገለግልበመሆኑያለመንምቅ ድመሁኔታመፅደቅእናመረጃንበማፈን፣ተጠያቂነትንየሚያፍኑእናየህዝብንጥቅምየሚጎዱአካላት ንበመከላከልብሄራዊመግባባትንማምጣትያስችላል፡፡በዚህም
በኢትዮጵያ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 29(3)(ለ) መረጃ የማግኘት መብትን በግልጽ የተረጋገጠውን ድንጋጌእንዲጠበቅእናበዋናነትችግርሁኖየቀጠለው የኢትዮጵያ መንግሥት የአስተዳደር ባህል በ አብዛኛው ሚስጥራዊ በመሆኑ ሥልጣንን ያላግባብ መጠቀምንና የሰብዓዊ መብቶች ጥሰት ማስከ

ተሉን በመረዳት፣ እንዲሁም የሕዝብ ጥቅምን የሚመለከቱ ጉዳዮች ግልጽ እንዲደረጉና ውይይት እንዲደረግባቸው ግልጽ የሆነ የሕግ ማዕቀፍ ማበጀት አስፈላጊ ነው፡፡

የመረጃነፃነትአዋጅቁጥር 590/2000 ዓ. ምላይእንደሰፈረውዜጎችመረጃየማግኘትሕገ-መንግስታዊመብትእንዳላቸውና**የመረጃ**ባለቤቶችመሆናቸውንይደነግጋል።**የመረጃነፃነት**ይዞትከ ተነሳውዓላማአንፃርበአግባቡቢተገበርበርካታጠቀሜታዎችእንዳሉትምተመልክቷል።ከጠቀሜ ታዎቹመካከልምግልፅነትናተጠያቂነትንማስፈን፤ሙስናናብልሹአሰራርንመከላከል፤ፍትህንማ ስፈንእንዲሁምየዜጎችመብትናጥቅሞችንማስከበርይጠቀሳሉ።

የመንግሥትና የግል አካላት ለግለሰቦችና ለመገናኛ ብዙኃን መረጃን ተደራሽ እንዲያደርጉ የሕግ ግዴታ ለመጣል፣ የሕዝብ ተሳትፎንና የሥልጣን ባለቤትነትን የማረጋገጥ፣ ግልጽነት፣ ተጠያቂነ ትና ውጤታማነት የሰፈነበት የመንግሥት አሠራርንና መልካም አስተዳደርን ለማጠናከር በመወ ሰንና የመረጃ ነፃነትን ማረጋገጥ አለበት፡፡

2. የኢንተርኔትመዘጋት፡- በፖለቲካ አለመረጋጋት ወቅት የኢንተርኔት መዘጋት የመረጃ ፍሰትን የሚገድብ እና ዲጂታል ጋዜጠኝነትን የሚያዳክም መደበኛ መለኪያ ሆኗል። በተለያዩ የሀገራቱ አካባቢዎች ግጭትን ተከትሎ የኢንተርኔት አገልግሎት መቋረጥ (2020-2024) ዘገባዎችን እና ሰብአዊ ጥረቶችን በከፍተኛ ሁኔታ አግዶታል።

3. ግልጽነት ማጣት፡- የመንግስት ባለስልጣናት ብዙ ጊዜ መረጃ ለመስጠት ፈቃደኛ ባለመሆናቸው ተጠያቂነትን ያዳክማል። ሪፖርቶች እንደሚያሳዩት ጋዜጠኞች በሕዝብ ወጪ እና አስተዳደር ላይ ወሳኝ መረጃዎችን በተደጋጋሚ እንዳያገኙ ይከለከላሉ (Open Government Partnership, 2021)።

ተጽዕኖ

- **የምርመራ ጋዜጠኝነት እንዳይሰፋፉ እንቅፋት መሆን።**
- **ሙስናን ያስፋፋል**

ተጠያቂነት እንዳይኖር ያደርጋል።

የመረጃ ሰርጭትን ይገድባል፡፡

• የተሳሳተ መረጃ እና የህዝብ አለመተማመንአሰፍኗል። የነዚህ ቁልፍ ችግር መፍትሄ በብሄራዊ የምክክር አጀንዳ ቢሸፈን አውንታዊ ተፅዕኖ ይኖረዋል፡፡

ምክሮች

1. የመረጃ ተደራሽነት ህጎችን ማውጣት፡ ከአፍሪካ ህብረት የመረጃ ተደራሽነት ሞዴል ህግ በማውጣት የህዝብን ተደራሽነት ለማረጋገጥ ጠንካራ የህግ ማዕቀፎችን ማዘጋጀት።

2. የኢንተርኔት መዝጋትን መከልከል፡ ብሄራዊ ፖሊሲዎችን ከሰላማዊ ተቃዋሚዎች አንፃር የሰብአዊ መብቶችን ማስተዋወቅ እና ከመሳሰሉ አለም አቀፍ ደረጃዎች ጋር ማጣጣም።በመገናኛብዙኃንአዋጅ 1238
ላይ በግልፅእንደተመለከተውየበይነመረብ ጋዜጠኞችናፈቃድ ያለውማንኛውምየሚዲያተቋምተመዝግቦህጋዊሰውነትእስካገኘድረስበመደበኛውመገናኛብዙሃንእናበበይነመረብ የሚተገበሩየአገልግሎት መድረክወይምፎርማት (ድረገፅ፤ዩቲዩብ፤ፌስቡክ፤ቲውተር፤ኢንስታግራም፤ሊንክዲንወዘተ)ሁሉንምሙያዊስነ-
ምግባርእናየጋዜጠኝነትዋናእሴቶችንእስካከበሩድረስገደብሊጣልባቸውአይገባም፡፡

3. ተደራሽየመረጃ አቅርቦትን ማሳደግ፡ የመንግስት ባለስልጣናትን በግልፅነት አሰራር ላይ ማሰልጠን እና መረጃን በወቅቱ ለማሰራጨት መድረኮችን ማዘጋጀት።

አጀንዳ 3፡ የፋይናንስ ዘላቂነት እና የማስታወቂያ ፍትሃዊነት

የአጀንዳው ፅንሰ ሃሳብ ፡- የፋይናንሺያልዘላቂነትእናየማስታወቂያፍትሃዊነት፡- ፍትሃዊየሀብትድልድልንማረጋገጥእናለሚዲያስራዎችፍትሃዊየፋይናንስአሰራር እንዲፈጠር በማስቻል በሀገሪቱ የሚሰተዋለውን ዋልታ ረገጥ የሚዲያዎች ጤናማ ያልሆነ የመረጃ ፉክክር ወደ ፍትሃዊ የመረጃ ስርጭት እንዲኖር በማስቻል የተዛነፈውን ብሄራዊ መግባባት ለማስተካከል የሚረዳ በመሆኑ፣ ውይይት ቢደረግበት በሀገሪቱ የሚሰተዋለውን የሚዲያ ተቃርኖ ፅንፍ በማሰወገድ የሚዲያ የሀገር ባለቤትነት እንዲረጋገጥ ድርሻ ይኖረዋል።

የአጀንዳው ማብራሪያ፤-

ለመንግስት ቁጥጥር ስር ብቻ ለሚገኙ መገናኛ ብዙሐን ከአምስት ቢልየን ብር የበለጠ ሃብት በየአመቱ በማስታወቂያ ሰበብ እና በፕሮግራም ዝግጅት ነፃ መገናኛ ብዙሐንን

በአገለለ ሁኔታ ለፖለቲካ ትርፍ ፈሰስ ይደረጋል፡፡ አዋጅቁጥር 759/2004 አንቀጽ 2(1) ስለማስታዎቂያትርጓሜየሕዝብአገልግሎት በሁሉም መገናኛ ብዙሐን ተደራሽ እንዲሆን ቢደነግግም የግል መገናኛ ብዙሐንን ያገለለ አሰራር አለው፡፡ኢትዮጵያእስከ 2004 ዓ/ምድረስማስታወቂያንበተመለከተወጥእናየተሟላየህግማዕቀፍያልነበራትቢሆንምስለብሮድካስ ትአገልግሎትየወጣውአዋጅቁጥር 533/1998 ማስታወቂያንበተመለከተከአንቀጽ 33 እስከ 36 የተደነገጉትንውስንድንጋጌዎችአካትቶይዟል፡፡

ይሁንናእኚህሃሳቦችማስታወቂያንበህግለመምራትናስርዓቱንበጠበቀመልኩእንዲከናወንለማድረ ግበቂናቸውሊባሉየሚችሉአይደሉም፡፡በዚህምመሰረትአዋጅቁጥር 759/2004 የማስታወቂያአዋጅ ዘርፉ እንዲቀጭጭ አድርጎታል፡፡ የአዋጅዋናአላማዎችገበያመርየሆነውየኢኮኖሚስርዓትጤናማበሆነውድድርእንዲመራአላደረግ ም፡፡
ማስታወቂያበህግስርዓትባለመመራቱምክንያትበህብረተሰቡላይሊደርስየሚችለውንየመብትናየ ጥቅምጉዳትለመከላለክልእንዲሁምየሀገርንገጽታሊያበላሹየሚችሉአደገኛማስታወቂያዎችንለ መከላከል አልቻለም፡፡
ነፃየሆነየማስታወቂያማስተላለፍስራየሚያስከትለውንበጎያልሆነተጽዕኖለመከላከልሲባልበማስታ ወቂያወኪልነት፣አስነጋሪነትእናአሰራጭነትየሚሳተፉሰዎችንመብትናግዴታግልጽበሆነአግባብበ መደንገግህግናስርዓትንየማስከበርሂደቱንውጤታማአለማድረግእና መንግስት የራሱን ጥቅም ብቻ ለማሰጠበቅ አውሎታል፡፡

ችግሮች በዝርዝር

1. ማስታወቂያዎችን በብቸኝነት እንደመረጃ ፍሰቱ ለአንድ ወገን ያደለ መሆን፡ የመንግስት ሚዲያዎች የማስታወቂያ ገቢዎችን በመቆጣጠር ለግል እና ለማህበረሰብ ሚዲያዎች እኩል ያልሆነ የመጫወቻ ሜዳ ፈጥረዋል። ከመንግስት ጋር የተቆራኙ ንግዶች የመንግስት ስሪት ባህሪ ያላቸው ማሰራጫዎችን ለማስታወቂያ ምደባ ቅድሚያ ይሰጣሉ፣ ገለልተኛ ድምጾችን ወደ ጎን በመተው ለአፈና መሳሪያ ሁኗል።

2. ፍትሃዊ ያልሆነ የሀብት ክፍፍል፡-የግል ሚዲያዎች በዋጋ ንረት እና የህዝብ ድጎማ ባለማግኘታቸው ለስራ ማስኬጃ ከፍተኛ ወጪ ይዳረጋሉ። ይህ የፋይናንሺያል አለመመጣጠን ውድድርን እና ፈጠራን አዳክሟል።

3. ገዳቢ የማስታወቂያ ሕጎች፡- ጊዜ ያለፈባቸው ሕጎች የግል ሚዲያዎችን ሚዛናዊ በሆነ መልኩ ይነካሉ። ለምሳሌ፣ በአልኮል ማስታወቂያ ላይ የሚደረጉ ገደቦች ለአነስተኛ ማሰራጫዎች የገቢ ጅረቶችን ይገድባሉ (ሚዲያ ህግ ክለሳ፣ 2021)።

ተጽዕኖ

• ለነጻ ሚዲያ የገንዘብ አለመረጋጋት።

• የተገደበ የሚዲያ ብዝሃነት።

• በፖለቲካዊ የተሳሰረ የገንዘብ ድጋፍ ላይ ጥገኝነት መጨመር።

ምክሮች

1. ተዘዋዋሪ ፈንድ ማቋቋም፡- ገለልተኛ እና የማህበረሰብ ሚዲያን ለመደገፍ በህዝብ የሚተዳደር ፈንድ መፍጠር ፍትሃዊ ውድድርን ማረጋገጥ።

2. የማስታወቂያ ህጎችን ማሻሻል፡ የማስታወቂያ ገቢዎችን ፍትሃዊ ተደራሽነት ለማበረታታት ደንቦችን ማዘመን።

3. አማራጭ የገንዘብ ድጋፍ ሞዴሎችን ማበረታታት፡ የገቢ ምንጮችን ለማብዛት የግል ኢንቨስትመንትን እና የገንዘብ ድጋፍን ማሳደግ።

አጀንዳ 4፡ ዲጂታል ትራንስፎርሜሽን እና ሚዲያ መሠረተ ልማት

የአጀንዳው ፅንሰ ሃሳብ፡-ዲጂታልትራንስፎርሜሽንእናየሚዲያመሠረተልማት፡-ቅልጥፍናንለማሳልበትእናለመድረስየሚዲያቴክኖሎጂዎችንማገናኘትእናማዘመን በተመለከተ አጀንዳ ተደርጎ ቢመረጥ በሀገራችን የሚታየውን የመረጃ ፍሰት ክፍተት፣ የሰው እና የሚዲያ ሃብት ልማት በማሳደግ ችግር ፈች ይሆናል፣ ጎዝቡም የገጠመውን የመረጃ ተደራሽነት ይፈታል። በመንግስት የተለያዩ ህጎች በቴክኖለጅዎች ላይ የሚጣለው ፍትሃዊ

ያልሆነ የቀረጥ ጥያቄ የህትመት እና ኤሌክትሮኒክስ መገናኛ ብዙሐን እንዳይስፋፉ በማድረግ ገዳቢ ሲሆን መረጃ መዘጋጀቱ ብቻ ሳይሆን ተደራሽነቱ ላይ እንቅፋት ሁኗል።

የአጀንዳው ማብራሪያ፡-

የመገናኛ ብዙሐን መሰረተ ልማቶች በህትመት እና ኤሌክትሮኒክስ ዘዴ ዘርፉን በሚደግፉ እና የሀገሪቱን ህዝቦች ተጠቃሚነት ባረጋገጠ መልኩ እየተከናወኑ አይደለም። በተለይም የህትመት ሚዲያዎች የወረቀት ታክስ ፣ የማተሚያ መሳሪያዎች ክልከላ፣ የሳተላይት ኪራይ፣ ዘርፉን ያቀጨጨ እና ፍትሃዊ ተወዳዳሪነት እንዳይኖር በማድረግ የሀሳብ ብዝሃነት እና ዴሞክራሲያዊ ተግባቦቶች እንዳይዳብሩ ችግር ሁኖ ተስተውሏል። በሀገሪቱ የሚሰተዋለው የሀሰተኛ መረጃ ስርጭት ፣ በመንግስት ብቻ የመረጃ ፍላጎት ፍሰት እንዲኖር እና ሀቅን በማጣራት ረገድ የራሱ ተግዳሮት እንዲኖረው አድርጓል።መገናኛብዙኃንሕዝብናመንግሥትንበማገናኘትናብልሹአሠራሮችንበማጋለጥከፍተኛድርሻቢኖራቸውምበአሁኑጊዜየኅትመትናሳተላይትክፍያዋጋመጨመርለተለያዩመገናኛብዙኃንሕልውናፈተናሆኗል። በአሁኑ ስዓት ዘርፉ በመንግስት በሚደረግበት በእውቀት ላይ ያልተመሰረተ ውሳኔ ምክንያት በዲጅታል ቴክኖለጅ ሀሰተኛመረጃበስፋት የሚናኝበት ሁኗል።

ሀሰተኛመረጃዜጎችበእውቀትላይየተመሰረቱውሳኔዎችንየመወሰንአቅማቸውንበማቀጨጭየዕለት ከዕለትእንቅስቃሴያቸውንያዛባል፣በአካባቢያዊእናሀገርአቀፍምርጫዎችበሚኖራቸውተሳትፎላ ይአለታዊተፅዕኖያሳርፋልእንዲሁምበማህበረሰቦችመካከልመከፋፈልንእናመካረርንበማስፋትለ ግጭትበርከፍቷል።የተወሰኑትንመገናኛብዙኃንምበዘርፉእንዳይቆዩእያደረጋቸውነው።ዋና ዋና ችግሮች በዝርዝር ስንመለከትም

1. የዲጂታል ክፍፍል፡ የጥላቻንግግርናየሐሰተኛመረጃስርጭትለመከላከልናለመቆጣጠርየወጣአዋጅ. አዋጅቁጥር 1185/2012ዓ.ም. የጥላቻንግግርናየሐሰተኛመረጃስርጭትለመከላከልናለመቆጣጠርየወጣአዋጅ ዋና ዓላማ ዜጎችስለሚዲያእናስለመረጃያላቸውንንቃትእናግንዛቤማሳደግ (media and information literacy) ሀሠተኛመረጃየሚያስከትለውንዘርፈብዙጉዳትለመግታትአይነተኛመፍትሄነው።ንቃትእናግንዛ ቤያላቸውዜጎችትክክለኛመረጃከየትማግኘትእንዳለባቸውያውቃሉ።ነገር ግንየገጠር

አካባቢዎች አስተማማኝ የኢንተርኔት እና የዲጂታል መሳሪያዎች አቅርቦት ስለሌለ ከፍተኛ ቁጥር ያለው ህዝብ ከአገልግሎት በታች እንዲሆን አድርጎታል፡፡ (አለም ባንክ፣ 2021)።

2. ጊዜው ያለፈበት ቴክኖሎጂ፡- ብዙ የሚዲያ ቤቶች ጊዜ ያለፈባቸው መሳሪያዎች ይሰራሉ፣የይዘት ጥራት እና ስርጭትን ይጎዳሉ (ዩኔስኮ፣ 2020)።

3. የሳይበር ደህንነት ስጋቶች፡ ጋዜጠኞች የመረጃ ጠለፋ እና ክትትልን ጨምሮ የዲጂታል ስጋቶች እየጨመሩ ነው። የኢትዮጵያ ጠንካራ የመረጃ ጥበቃ ህጎች እጦት ይህንን ጉዳይ ያባብሰዋል (ሳይበር ሴክዩሪቲ አፍሪካ፣ 2022)።

ተጽዕኖ

• የሚዲያ ስራዎች ውስን ተደራሽነት።

• ጥራት የሌለው ጋዜጠኝነት።

• ለዲጂታል ጥቃቶች እና የተሳሳቱ መረጃዎች ተጋላጭነት።

ምክሮች

1. የብሮድባንድ መሠረተ ልማትን ማስፋፋት፡- በገጠር ግንኙነት ላይ በመንግሥትና በግል አጋርነት ኢንቨስት ማድረግ።

2. የሚዲያ ቴክኖሎጂን ማሻሻል፡ ለዘመናዊ መሳሪያዎች እርዳታ መስጠት እና ለሚዲያ ባለሙያዎች የስልጠና ፕሮግራሞችን መስጠት።

3. የሳይበር ደህንነትን ማሻሻል፡ የመረጃ ጥበቃ ህጎችን ተግባራዊ ማድረግ እና ጋዜጠኞችን በዲጂታል ደህንነት ተግባራት ላይ ማሰልጠን ያሰፈልጋል።

አጀንዳ 5፡ የጋዜጠኞች ደህንነት እና ደህንነት

የአጀንዳው ፅንሰ ሃሳብ፡- የጋዜጠኞችደህንነትእናደህንነት፡- ጋዜጠኞችንበአካላቸው፣ በስነልቦናቸው፣ የተለያዩ አካለት ህግን እንደማጥቂያ መሳሪያ በመጠቀም፣ እና በስራቸው ምክንያት ነፃነት በማጣት ዛቻ፣ ማስፈራራት፣ ጥቃትእና የዲጂታልስለላዎች ተጋላጭ

ሁነዋል፡፡ በሚደርስባቸው እስር ፣ እንግልት ፣ አፈና ፣ ስወራ እና ግድያ ምክንያት ስራቸውን በፍራቻ የሚሰሩ፣ በምርመራ ዘገባዎቻቸው ምክንያት ለጥቃት የተጋለጡ በመሆኑ ፣ ደህንነታቸውን የማሰጠበቅ እና ነጻእናገለልተኛ መገናኛ ብዙሐን እንዲፈጠር የፖለቲካ ምህዳሩ እና ማህበረሰቡ ጋር የውይይት አጀንዳ ቢሆን በዚህ ችግር መፈታት ብዙ የማህበረሰብ ችግሮችን ይፈታሉ ብለን ስለተስማማን የብሄራዊ ምክክሩ አጀንዳ አድርገን መርጠነዋል።

የአጀንዳው ማብራሪያ፡- በመገናኛብዙኃንአዋጅ 1238/13 አንቀፅ 86 ንዑስአንቀፅ 1 ላይበግልፅእንደተመለከተውበመገናኛብዙሃንአማካይነትየወንጀልድርጊትበመፈፀምየተጠረጠረ ማንኛውምሰውወይምአካልበወንጀልሥነ-
ሥርዓትየሕግድንጋጌዎችመሠረትለተጨማሪምርመራበእስርእንዲቆይሳይደረግክሱበቀጥታበዓ ቃቤሕግአማካኝነትለፍርድቤትመቅረብእንዳለበትተደንግጓል።ሆኖምየሀገሪቱከፍተኛየሕግአው ጭአካልየሆነውየህዝብተወካዮችምክርቤትያወጣውይህአዋጅሀሳብንበነፃነትየመግለፅመብትንይ በልጥለማስፋትናሙያተኞችበሃላፊነትስሜትእንዲሰሩለማበረታታት ያለመቢሆንም ከሕጉመን ፈስተቃራኒበሆነመንገድየዜጎችመብትበፍትሕአካላትበተደጋጋሚእየተጣሰነው፡፡በሚዲያአማካ ኝነትተፈጽሟልበተባለወንጀልተጠርጣሪየሆኑጋዜጠኞችበፖሊስሲያዙብቻሳይሆንፍርድቤትሲ ቀርቡምበአዋጁመሠረትያለመሆኑ ባለሙያዎችስራቸውንበነጻነትእንዳይሰሩ፤እንዲሸማቀቁናየ ፕሬስምህዳሩየበለጠእንዲጠብአድርጎታል፡፡ጋዜጠኞችንበተመለከተከሕጉአግባብውጪየሚፈፀ ሙህገወጥድርጊቶችንለማስቀረትያለመቻሉምክርቤታችንንአጀንዳ እንዲሆን በዋና የምክክር ርዕሰ ጉዳይነት ለይቶታል፡፡

ጋዜጠኞችመካከልአንዳንዶቹፍርድቤትቀርበውየጊዜቀጠሮየተሰጣቸውቢሆንም፤አሁንምፍርድ ቤትያልቀረቡናየታሰሩበትቦታየማይታወቁጋዜጠኞችመኖራቸው ፤
ከሕግውጭ ከመያዛቸው፤ባሻገር ፍርድቤትሳይቀርቡክስሳይመሰረትባቸታስረውመቆየታቸው፣ያ ለበትንመደበቅእናበቤተሰብናየሕግባለሞያእንዳያገኙ መከልከልየመገናኛብዙኀንአዋጁንየሚፃ ረርተግባርነው፡፡
በየግዜውየሚታየውየጋዜጠኞችእስራትእናእንግልትየሕግከለላአለማግኘትበሀገራችንሀሳብንበነፃ ነትየመግፅመብትንጥያቂውስጥከመክተቱምባሻገር በሞያውላይያሳደረውንተፅኖክፍተኛ ነው፤፤
በዝርዝር የተመላከቱ ችግሮችም የሚከተሉት ናቸው፡፡

1. **አካላዊ፣ ስነ ልቦናዊ እና ህጋዊ ጥቃት፡-** ጋዜጠኞች በተደጋጋሚ ጥቃት፣ እስራት እና ማስፈራራት ይደርስባቸዋል። በፀረ-ሽብርተኝነት ሕጎች የጋዜጠኞች መታሰር ቀጣይነት ያለው ጉዳይ ነው (የጋዜጠኞች ጥበቃ ኮሚቴ፣ 2022)። እነዚህ ድርጊቶች የምርመራ ጋዜጠኝነትን እና ሂሳዊ ዘገባዎችን የሚያበረታታ የፍርሃት ሁኔታን በማጎልበት በፕሬስ ነፃነት ላይ የረጅም ጊዜ አንድምታ አላቸው። በተጨማሪም ጋዜጠኞች ራሳቸውን ችለው መንቀሳቀስ እንደማይችሉ ሲታሰብ ህዝቡ በመገናኛ ብዙሃን ላይ ያለው እምነት እየቀነሰ ይሄዳል፣ ይህም በቂ መረጃ የሌለው ዜጋ እና ደካማ ዴሞክራሲያዊ ተጠያቂነት እንዲኖር ያደርጋል።

2. **የህግ ትንኮሳ፡-** አሻሚ ህጎች ተቃውሞን ለማፈን ፣ በትችት ላይ የተመሰረተ ዘገባ እንዳይሰራ ፣ በምርመራ ጋዜጠኝነት ተመስርተው በደሎች እና የህግ ጥሰቶች እንዳይጋለጡ በማድረግ ስራቸውን ለመመሰራት እና ኃላፊነት ለመወጣት የሚሞክሩትን ጋዜጠኞች የዘፈቀደ እስር በመዳረግ በፍራቻ ከሙያቸው እንዲወጡ፣ የህዝብን ጥምቅ እንዳያሰጠብቁ እና ከሀገር እንዲሰደዱ ምክንያት ሁኗል።

3. **ያለመከሰስ መብት አለመከበር፡-** ጋዜጠኞች ሚስጥራዊነት ባላቸው ጉዳዮች ላይ ሲዘግቡ የህግ ከለላ ስለሌላቸው ሰፊ ራስን ሳንሱርን እንዲያደርጉ ተገደዋል (የኢትዮጵያ ሚዲያ ካውንስል ሪፖርት፣ 2022)።

በነዚህ ዋና ዋና ጉዳዩች ምክንያት የሚከተሉት ተጽዕኖ ደርሰዋል፡፡

- የምርመራ ጋዜጠኝነት መቀነስ።
- በጋዜጠኞች መካከል ፍርሃት እና ራስን ሳንሱር ማድረግ።
- የህዝብ ተጠያቂነት ቀንሷል።

ምክሮች

1. **የሀገሪቱን ህጎች እና ዓለም አቀፍ ስምምነቶችን የሚያከበር የፖለቲካ ስርዓት መገንባት አለበት፡-** ኢትዮጵያ የጋዜጠኞችን ደህንነት በተመለከተ የሀገሪቱን ህጎች እና የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የድርጊት መርሃ ግብር የሚቀበል እና የሚከብር ስርዓት ያስፈልጋል።

2. የፕሬስ ደህንነት ጥበቃ አካል ማቋቋም፡- በጋዜጠኞች ላይ የሚደርሱ ስጋቶችን ለመፍታት ፈጣን ምላሽ ሰጪ ዘዴ እንዲፈጠር የጋዜጠኞች ከለላ እና ደህንነት ጥበቃ እውቅና የሚሰጥ የፖለቲካ ኃላፊነት ይፈለጋል።

3. በስራቸው ምክንያት ያለመከሰስ መብት ማረጋገጥ፡- ጋዜጠኞችን በህጋዊ ዘገባ በተለይም በእርስ በርስ ቁጥጥር ስር ብቻ እንዲያልፉ መንግስትን ጨምሮ ኃላፊነቱን መወጣት አለበት፡፡

ማጠቃለያ፡ የኢትዮጵያ ሚዲያ ካውንስል ስትራቴጂካዊ ሚና

የኢትዮጵያ ሚዲያ ካውንስል እነዚህን ማሻሻያዎች ሊመራው የሚገባው፡-

1. የሚዲያ ማሻሻያዎችን በሀገር አቀፍ የውይይት ማዕቀፍ ውስጥ እንዲካተት አጀንዳዎቹን ያቀርባል ።

2. በመገናኛ ብዙኃን የሚደረጉ ውይይቶችን ማመቻቸት ትረካዎችን ከሀገራዊ ጥቅሞች ጋር እንዲጣጣሙ ይጠይቃል።

3. ለአቅም ግንባታ ከባለደርሻ አካላት ጋር በመተባበር ለመስራት ቁርጠኝነቱን ያሳውቃል።

4. ዜጎችን ለማብቃት እና ወሳኝ ተሳትፎን ለማነልበት የህዝብ የሚዲያ እውቀትን ለማሳደግይሰራል።

እነዚህን ጉዳዮች ሁሉን አቀፍ በሆነ መልኩ በመፍታት ኢትዮጵያ የሚዲያ ምህዳሯን ወደ ጠንካራ፣ ገለልተኛ እና ዲሞክራሲያዊ ተቋም ወደ እርቅ፣ አንድነት እና ዘላቂ ልማት የሚደግፍ ተቋም ማድረግ ትችላለች።